# የግል መረጃዎን ከCrisis ጋር መጋራት:

- እኛ የእርስዎን ዝርዝር የግል መረጃ ለምን እንጠይቃለን
- በመረጃዎቹ ምን እናደርጋለን
- መብቶችዎን መረዳት

## ለምን መረጃዎን እንደምንጠይቅ እና እንደምናስቀምጥ

Crisisን እርዳታ ሲጠይቁ እና እንደ አባል ሲቀላቀሉን የተወሰኑ የግል መረጃዎችን እንጠይቅዎታለን፡፡ ይህ መረጃ ለእኛ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም ቤት በተሳካ ሁኔታ እንዲያገኙ የሚፈልጉትን ድጋፍ ለእርስዎ ለመስጠት ከእርስዎ ጋር አብረን እንድንሠራ ይረዳናል፡፡

እንዲሁም አገልግሎቶቻችን ውጤታማ (በጥሩ ሁኔታ እየሰሩ) መሆናቸውን ለማረጋገጥ የእርስዎን መረጃ እንጠቀማለን፡፡

መረጃዎን የምንጠቀምበት ሌላው መንገድ ፖሊሲዎችን ለመለወጥ እና ለወደፊቱ የቤት እጦትን ለመቀነስ ስራችንን እንዲያግዜን ነው፡፡ እኛ መረጃዎን በዚህ መንገድ በምንጠቀምበት ጊዜ እርስዎ በማንነትዎ አይለዩም።

የተወሰኑ ነገሮችን ሲነግሩን ምቾት የማይሰማዎት ከሆነ መረጃ መስጠት አይጠበቅብዎትም። ነገር ግን ሁሉንም አገልግሎቶቻችንን ለመጠቀም ከፈለጉ ለእኛ መስጠት ያለብዎት የተወሰነ መረጃ ይኖራል፡፡

የCrisis አባል ሲሆኑ ከእኛ ጋር ወደ አንድ ጉዳይ ዝግጅት ይገባሉ። እርስዎን ከቤት አልባነት ፈጽሞ እንዲላቀቁ ለመደገፍ እኛ እርዳታ እና ምክር እንሰጥዎታለን። በምላሹም፣ እኛ ትክክለኛውን እርዳታ ለእርስዎ ለመስጠት የሚያስፈልገንን መረጃ ይሰጡናል።

ይህ እርስዎ ለእኛ መረጃ የሚሰጡበት እኛ ደግሞ ለእርስዎ እርዳታ እና ድጋፍ የምንሰጥበት፣ ዝግጅት፣ እንደ የኮንትራት “ውል” ሊቆጠር ይችላል። ከእንግዲህ በዚህ ዝግጅት መቀጠል ሳይፈልጉ ሲቀሩ ይህን ለኛ ሊነግሩን ይችላሉ።

በሕጉ መሠረት፣ Crisis ስለ እርስዎ እና ስለ ሌሎች አባላት መረጃ ለመሰብሰብ እና ለማስኬድ ሕጋዊ መሠረት ሊኖረው ይገባል፡፡ ሕጋዊነት ያለው መሰረት የሚያጠቃልለው፣ ፖሊሲን ለመለወጥ እና አገልግሎቶቻችንን የተሻለ እንዲሆን ዕገዛ ማድረግን አክሎ፣ እኛ እንደ አንድ ድርጅት ሥራችንን በአግባቡ እንድንሠራ መረጃ የመጠየቅ ፍላጎታችን ጭምር ነው። ይህ በቴክኒካዊ መልኩ “ሕጋዊ የሆነ ፍላጎት” በመባል ይታወቃል።

በተጨማሪም የእኛ ኮንትራት “ውል” ዝግጅት የእርስዎን መረጃ እንድንሰበስብ እና እንድናከናውን ሕጋዊነት ያለው መሠረት ይሰጣል።

በመጨረሻም፣ የሰዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ያግዘን ዘንድ፣ የተወሰነ መረጃ መሰብሰብ ለእኛም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ “ወሳኝ የሆኑ ፍላጎቶች” በመባል ይታወቃል።


Crisis UK (trading as Crisis). Registered Charity Numbers: E&W1082947, SC040094. Company Number: 4024938.

## መረጃዎን እንዴት በደህንነት እንደምናስቀምጠው

እርስዎ የሚሰጡን መረጃ - የእርስዎ ‘መረጃ’ - በወረቀት ላይም ይሁን በኮምፒዩተር ስርዓታችን ላይ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው። መረጃዎ በእኛ የCrisis ቡድን አባላት ለእርስዎ የሚሰሩትን ሥራ ለማገዝ ሲባል በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ይውላል።

ፍላጎቶችዎን ለመደገፍ የተሻለ ቦታ ካላቸው፣ ስለ እርስዎ የተወሰነ መረጃ ለሌሎች ድርጅቶች ልናጋራ እንችላለን፣ ነገር ግን እኛ ሁሌ ይህንን የምናደርግ ከሆነ ፈቃደኝነትዎ ፍጹም አስፈላጊ በማይሆንበት ሁኔታ ላይ እንነግሮታለን። በተባበሩት ብሪጣኒያ (UK) ሕግ መሠረት፣ ከCrisis ውጭ ከማንም ወይም ከማንኛውም ድርጅት ጋር ሚስጥራዊ መረጃዎን (ለምሳሌ፣ በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩትን ጤንነትዎን እና ሌሎች መረጃዎችን የተመለከተ) ከሚከተሉት ሁኔታዎች በስተቀር እርስዎን አስቀድመን ሳንጠይቅ ማጋራት አንችልም:

- ለጉዳት ተጋላጭነት አለው ብለን የምናምንበትን ማንኛውም ሰው (እርሶን ጨምሮ) ደህንነት እና ጤንነት ለመጠበቅ ሲባል መረጃን ማጋራት አለብን።
- ፖሊስ የከባድ ወንጀል ምርመራ ላይ እንድንተባበር ከጠየቀን ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መረጃ እንድናስረክብ ከተጠየቅን መረጃውን ማጋራት ይኖርብናል።

## የእርስዎ የስምምነት ዕውቅና ፈቃድ አስፈላጊ ነው

ያለ እርስዎ የዕውቅና ስምምነት ፈቃድ የተወሰኑ መረጃዎችን ወደ እኛ የውሂብ ጎታዎች ላይ ማከል አንችልም። ይህ መረጃ የሚከተሉትን ያካትታል:

- የእርስዎ የዘር ወይም የብሔር ምንጭ
- የጤና መረጃዎ
- የእርስዎ ሃይማኖታዊ እና ፍልስፍናዊ እምነቶች
- የእርስዎ ወሲባዊ ዝንባሌ
- የባዮሜትሪክ መረጃ (ምንም እንኳን እኛ በአሁኑ ጊዜ እንደ ጣት አሻራዎች ያሉ ነገሮችን ጨምሮ እንዲህ ዓይነቶቹን መረጃዎች ባንሰበስብም)

እንደዚህ ዓይነቱን መረጃ በእኛ የውሂብ ጎታ ላይ ለማከል ሁልጊዜ የእርስዎን የስምምነት ዕውቅና ፈቃድ እንጠይቃለን።

ህጉ አይጠበቅብንም እስካላለ ድረስ፣ እሱን ለመጠቀም ወይም በድንገተኛ ጊዜ ጤንነትዎን ለመጠበቅ እንዲጠቀሙበት እኛ የእርስዎን ፈቃድ ሁልጊዜ እንጠይቃለን።

ሌሎች ማንኛቸውንም መረጃዎ ከሰበሰብንበት በተለየ ምክንያት የእርስዎን መረጃ መጠቀም ካስፈለገን፣ ለምን እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እናሳውቅዎታለን። ለምሳሌ፣ መረጃዎን በምርምር ወይም በፖሊሲ ሥራችን ውስጥ ማንነትዎን ለመለየት በሚያስችል መንገድ ለመጠቀም ከፈለግን፣ እንደሁልጊዜው በመጀመሪያ የእርስዎን ፈቃድ በማረጋገጥ እንጠይቅዎታለን።

የSkylight ወይም የCrisis ካፌን ሲጎበኙ በCCTV ሊቀረፁ ይችላሉ፡፡ እኛ CCTVን የምንጠቀምበት ምክኒያት ከእኛ ጋር የሚሰሩ ወይም የሚጎበኙን ሰዎች ጤንነታቸውን እና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ፣ ከዚህም አልፎ በአካባቢያችን የሚከናወነውን ማንኛውንም የወንጀል እንቅስቃሴ ለመከላከል እና ለማጣራት ነው። እኛ ይህንን የምናደርግ ከሆነ (በህንፃዎቻችን ውስጥ ባሉ ምልክቶች በኩል) ሁልጊዜ እንነግርዎታለን፡፡

## የእርስዎን መረጃ ስንሰበስብ

የሚሰጡን መረጃ ከእኛ ጋር በሚኖርበት ጊዜ በኮምፒተር የውሂብ ጎታዎች ላይ ይሰበሰብ እንዲሁም ይዘመናል።

የመረጃ አሰባሰብ ደረጃዎች በተለምዶ:

- ለመጀመሪያ ጊዜ እኛን ሲቀላቀሉ እና ከእርስዎ ጋር መስራት ስንቀጥል
- ኮርሶችን ከእኛ ጋር ሲወስዱ ወይም አገልግሎቶቻችንን ሲጠቀሙ
- እርስዎ የራስዎ የሆነ አስተማማኝ ቤት ሲያገኙ
- እርስዎ ከእንግዲህ የእኛን ድጋፍ እንደማይፈልጉ ሲወስኑ
- ከአገልግሎቶቻችን ከወጡ በኋላ እና ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልግዎት ለመፈተሽ ብሎም ስለእርስዎ መዝገቦችን ማዘመን እንድንችል መረጃዎን ለማጋራት ከተስማሙ

## መረጃዎን እንዴት እንደምንሰበስብ

እኛ የምንይዛቸውን አብዛኞቹን መረጃዎች እርስዎ ይሰጡናል። ነገር ግን አብረዋቸው የሚሰሩት የCrisis ሰራተኞች - ለምሳሌ፣ የእርስዎ አመራር ሰራተኛ - እንዲሁ በእኛ የውሂብ ጎታዎች ላይ ስለእርስዎ መረጃ ሊጨምር ይችላል።

ከCrisis ውጭ የተሳተፉባቸው ድርጅቶች፣ እንደ ሌላ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የእንግዳ ማረፊያ አቅራቢ፣ የምክር ማዕከላት፣ የአከባቢ ባለሥልጣናት ወይም በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ኤጀንሲዎች ለምሳሌ የአመክሮ አገልግሎት፣ ስለ እርስዎም ለእኛ መረጃ ይሰጡናል። መረጃው ካልተላለፈ ወይም ኤጀንሲው የማካፈል ሕጋዊ ግዴታ ከሌለው በስተቀር፣ እርስዎን ወይም ሌላ ሰው ከሚደርስባችሁ ጉዳት ለማዳን ሲባል ይህ መረጃ በእናንተ ፈቃድ እና ስምምነት ብቻ ነው የሚጋራው።

## ስለእርስዎ የምንይዛቸው የመረጃ ዓይነት

የምንጠብቃቸው የመረጃ ዓይነት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል:

- የአድራሻዎ ዝርዝሮች (አድራሻ፣ ስልክ እና ኢሜል)
- ከእኛ ስለፈለጉት የእርዳታ አይነቶች መረጃ - እና ምክንያቶቹ
- ስለ አካላዊ እና አእምሯዊ ጤንነትዎ መረጃ - ይህ የእኛን የጤንነት እና የደህንነት ጥበቃ መመሪያዎች እና ግዴታዎችን ለመታዘዝ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል
- ከእርስዎ ጋር ወይም ስለእርስዎ መገናኘት - ለምሳሌ ይህ  ስለ እርዳታዎች መብት ለእርስዎ የመጡ ደብዳቤዎች ሊሆን ይችላል
- እርስዎ ለመጠየቅ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ወጪ የሚደግፍ መረጃ
- እርስዎ የስቴት ጥቅሞችን የማግኘት ብቁነትዎ
- የቅርብ ተጠያቂ ዘመድዎ እና የአደጋ ጊዜ ዝርዝር መረጃዎ
- የዜግነት መረጃዎ
- የብቃት እና የሥልጠና መዝገቦችን ጨምሮ ስለ የቀድሞ ሥራዎ መረጃ
- የችሎት ፍርድ ጊዜአቸው ያልፈጸሙ የወንጀል ጥፋቶች ወይም እርስዎ የወንጀል ሰለባ በሆኑበት ቦታ
- እርስዎን በሚደግፉ የCrisis ሰራተኞች ስለ ተሰሩ ሰነዶች እና ኢሜሎች

## መረጃዎን ለምን ያህል ጊዜ እንይዛዋለን

አገልግሎቶቻችንን መጠቀም ካቆሙ በኋላ አብዛኛዎቹን የግል መረጃዎችዎን እስከ ሁለት ዓመት ድረስ እንይዛቸዋለን፡፡ አንዳንድ ጊዜም ረዘም ላለ ጊዜ ማቆየት ሊኖርብን ይችላል። ይህ ያልተለመደ ነገር ነው፣ ነገር ግን አንዳንድ ድርጅቶች እርስዎ የሚጠቀሙባቸውን አገልግሎቶች በገንዘብ የሚደግፉ ከሆነ፣ የመረጃ ዝርዝሮችን ረዘም ላለ ጊዜ እንድናቆይ ሊጠይቁን ይችላሉ።

የሁለት ዓመት ጊዜው ሲያልቅ፣ የግል መረጃዎን ስም-አልባ እናደርግ እናም የቤት-አልቦነት መንስኤዎች እና ሰዎች ከቤታቸው እንዲወጡ በሚያደርጉት ሰበቦች ላይ የምናደርገው ጥናት እና ምርምራችንን ለመቀጠል እንድንችል በዚህ መለያ-በሌለው ቅርጸት ተይዞ ይቆያል።

## መብቶችዎ እና መረጃዎ

መረጃዎ (ውሂብዎ) ጥቅም ላይ እንዴት እንደሚውል በተመለከተ መብቶች እና የመቆጣጠር ችሎታ አለዎት። ይህንን እንዲያደርጉ የሚረዱዎት ህጎች የUK አጠቃላይ የመረጃ ጥበቃ ደንብ (GDPR) እና የውሂብ ጥበቃ ሕግ 2018 (DPA) ናቸው፡፡

እነዚህ ህጎች ማለት:

- እኛ ስለእርስዎ ያለንን መረጃ በሙሉ እንድናሳይዎት እርስዎ ሊጠይቁን ይችላሉ
- እርስዎ ስህተት ነው ብለው የሚያስቡትን ማንኛውንም ነገር እንድናስተካክል ሊጠይቁን ይችላሉ
- የግል መረጃዎን ከስርዓቶቻችን እንድናጠፋ እርስዎ ሊጠይቁን ይችላሉ - ሆኖም ግን፣ እኛ ይህንን ለማድረግ የማንችልበት ጊዜ ሊኖር ይችላል፤ ለምሳሌ፣ ለእርስዎ የጉዞ ወጪዎች ተመላሽ ያደረግን ከሆነ፣ ለእርስዎ ያደረግናቸውን ክፍያዎች ዝርዝር በሕጋዊ መንገድ ማስቀረት አለብን
- በመረጃዎ የአሰባሰብ እና የማቀነባበር ምክንያቶቻችን ደስተኛ እንዳልሆኑ ሊነግሩን ይችላሉ
- የሚቻል ከሆነ (እና ውስን በሆኑ ሁኔታዎች) መረጃዎ ለሌላ ተመሳሳይ አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት እንዲተላለፍ መጠየቅ ይችላሉ
- ሃሳብዎን መለወጥ ይችላሉ - መረጃዎን ለማስኬድ እና ለማቆየት ፈቃድ ሰጥተውናል፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከዚህ ፈቃድ መውጣት ይችላሉ
- የ GDPR ወይም የ DPA 2018 ሕጎችን ጥሰናል ብለው ካመኑ ቅሬታዎችን ማቅረብ ይችላሉ፡፡

### ቅሬታን እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል

ስለ መረጃ ጥበቃ ቅሬታዎች በመንግስት የኢንፎርሜሽን ኮሚሽነሮች ጽ/ቤት ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡ እነሱን በ https://ico.org.uk/concerns/handling/ ሊያገኙዋቸው ይችላሉ

ነገር ግን፣ እኛ ሁልጊዜ እርስዎን መጀመሪያ ለመርዳት ለመሞከር እንፈልጋለን። ስለዚህ የመረጃዎ አያያዝ ላይ Crisis እያደረገ ያለው ተገቢ አይደለም ብለው የሚያስቡ ከሆነ እና ደስተኛ ካልሆኑ፣ እባክዎን በ Skylight ማዕከልዎ የመጀመሪያ ዕርዳታ እንዲያገኙ ዳይሬክተሩን ያነጋግሩ

የእኛ የመረጃ ጥበቃ መኮንን ቤቨርሊ አዳምስ-ሬይኖልድስ እንዲሁ ልትረዳ ትችላለች። ቤቨርሊ የምትገኘው በለንደን ዋና መስሪያ ቤታችን ውስጥ ነው። የእሷ ኢሜይል: data.protection@crisis.org.uk ነው

ሕጋዊ ማስታወቂያ: Crisis ለ DPA 2018 እና ለUK GDPR ዓላማዎች የውሂብ የመረጃ ተቆጣጣሪ ነው።